PANORAMA # ONE

## የትዝብት አድማስ

**ሕዳር** 13 2000

## የሞራል ጥያቄ

ሰበዓዊ ፍጥር የሆነ ሁሉ ከማነኛቸውም ህይወት ካላቸው ተንቀሳቃሾች የተለየ የሚያደርገውና የሰብዕናውንም ማንነት ከሚገልፅበት ዓበይትና መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ፥ የሞራል ጥያቄ  መሆኑ የሚያከራክር አይመስለንም፡፡ ይህም የሞራል ጉዳይ የሰውን ልጅ ሰብዕና ከሚያስከብርለትና ሞገስንም ከሚያተርፍለት መስፈሪያ የመጀመሪያውን ገፅ ይይዛል፡፡ የሞራል ጥያቄን ጉዳይ ስናወሳ፥ ታላላቅ ሃይማኖቶችና ፍልስፍናዎች ከሚሰብኩትና ከሚገልጹት አኳያ ብቻም አይደል፡፡  የሰው ልጅ በማኅበር መኖር ከጀመረበት አንስቶ ከማኅበረሰቡ ጋር የሚተሳሰርበት፥ የሚዛመድበት፥ የሚኖርበትና፥ ብሎም የተዛምዶ ልውውጥ ሊያደርግ የሚችልበትና ባኅላዊ መስተጋብሩን የሚገልጽበት ሁሉ ሲካተት፥ በሞራል ጥያቄ ዙሪያ የሚሽከረከር ይመስለናል፡፡

ሞራል ሲባል በደግነትና በክፉነት፤ በርኅራሄና በጭካኔ፥ በንፍገትና በቸርነት፥ በድፍረትና በፍርሃት፥ በነውርና በጨዋነት እና በመሳሰሉት የሰውን ልጅ ባኅርያት ሊገልጹ በሚችሉ የጥንድ ንፅፅር ብቻ ተወሰኖ የሚታይ ሊሆንም አይገባውም፡፡  የሞራል ጥያቄ መታየት ያለበት፥ ሁለንተናዊ ይዘትን ባካተተ የማኅበራዊ ክስተትንና ሂደትን ሁሉ ከሚዳስስና ከሚገመግም ሚዛን አኳያ  ሊሆን ይገባል፡፡  ጠቅላላ የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊ ባኅሪ መግለጫ ነው ቢባልም ትርጉሙ ተለጥጧል ለማለት የሚቻል አይመስልም፡፡

ከሞላ ጎደል፥ በዚህ ግንዛቤ መግባባት ከተቻለ፥ አባላትን ከድርጅት፥ ድርጅትን ደግሞ ከጠቅላላው የሕዝብና የሀገር ጉዳይ ጋር ሊያስተሳስረው፥ ሊያገናኘውና ሊያስተማምነው የሚችለው መሠረታዊ ሃብል  ዕምነት ነው፡፡ መተማመን ነው፡፡ ከሰነዶች፥ ከድርጅት ፕሮግራሞች፡ ከጋራ መግለጫዎች፥  በሀገሮች መካከል የሚከናወኑ የስምምነት ፊርማዎች፥ በባልና ሚስት መካከል የሚፈረሙ የጋብቻ ሰማኒያዎችና ሌሎችም ቋሚና ብሔራዊ ሰነዶች አኳያ ሲታይ  መሠረተዊና ዘላቂ ሕይወት  ሊኖረው የሚችለው፥ መተማመን ሲኖር ብቻ ነው ማለትን እንፈልጋለን፡፡  ዕምነት ማነኛቸውም ሞራልን አጅበው የሚመጡ ሌሎች የሰው ልጅ ባኅርያትን ሁሉ ያስራቸዋል፡፡ “የሺ ልጥ ማሰሪያው ልጥ” እንዲሉ፥ የጀመሩትን የጋራ ዓላማ በጋራ ግብ ለማድረስ ከተፈለገ፥ በግድ የጋራ መተማመን አማራጭ አይኖረውም፡፡
“  ሰነድና ፊርማ ጠፊ ነው ተቀዳጅ፥ መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ” የተባለውም ይህንን የሰውን  ልጆች የሞራል  ልዕልናና የባኅርይ  ታለቅነት ለመመዘንና ለመግለጽ የሚያመልክት ይመስለናል፡፡  ሞራል በወታደራዊ ሳይንስ መዝገበ-ቃላት ሲተረጎም፥ አንድ ሠራዊት የውጊያ ብቃትን፥ አይበገሬነትንና ያመቸነፍን እንጅ የመቸነፍን ጠባይና ምልክት የማያሳይት ዝንባሌና ፍንጭ የማያመለክት ማለት ነው፡፡ ሠራዊቱ የሞራል ብቃቱ ከፍተኛ ነው የሚባለው ለዚሁ ነው፡፡ የጠላት ጦር፥ በመሳሪያ ጥራትም ሆነ በሰው ኃይል ብዛት ፥ በወጊያው ስልትና ቦታ የበላይነት ሊኖረው ቢችልም፥  ሠራዊቱ የሞራል ጥንካሬና ልዕልና ከሌለው፥ ተቃራኒው ተዋጊ ሰራዊት በከፍተኛ የሞራል ኃይል ገትሮ ከተዋጋ የማቸነፉ

ዕድል ከፍተኛ ይሆናል:: ይህ በውጊያ የሞራል የበላይነት ያለው ሠራዊት፥ ብዛት ያለውን የጠላት ሠራዊት በመሃል ሰንጥቆ በመግባት ጃርት የበላው ዱባ በማስመሰል ቀርድዶ ቀርድዶ ይጠለዋል:: በትግል ላይ ያለ ድርጅትም ይሁን በውጊያ ላይ የተሰለፈ ሠራዊት ምንም የተለያዩ ችግሮችና ፈተናዎች ቢገጥሙት የተነሳበትን ዓላማና ግብ መሠረት አድርጎ በፅናት እስከ መጨረሻው ይታገላል እንጅ በቀላሉ አይንበረከክም:: ብኩርናውንም መጭብጥ ምስር አይለውጥም:: ታሪኩንም አያበላሽም:: የጦር ባልደረቦቹንም ሆነ የትግል ጓዶቹን አይከዳም:: አጋልጦ አይሰጥም:: ይህንን የሚያደርግ ካለ ግን፥

> " እዚህ መጥተሽ በላሽ፥ እዚያም ሄደሽ በላሽ፥
> ሰው ታዘበሽ እንጅ ሆድሽን አልሞላሽ:: "

እየተባለ ይዘበትበታል:: ለዘለዓለም!

በኢሕአፓ ስር ተሰባስበውና ተደራጅተው በመታገል ለቆሙለት ዓላማ የመጨረሻውን ከፍተኛ መሥዋዕት የከፈሉትም ሆኑ፥ አሁንም የገቡበትን ቃል ኪዳን አክብረው በመታገል ላይ ያሉት አባላት በጋራ ሊያስተባብራቸው የቻለው፥ በመካከላቸው እንደ ብረት የጠነከረ መተማመን ስለነበራቸውና ስለአላቸው ነው:: ይህ ትግሉን ከዳር ለማድረስ የሚስችላቸው የጋራ መተማመናቸው፥ የሞራል እሴት፥ የሰብዕና ክብርና የመርሃ-ግብር( የፕርንስፕል) አጀብ እንዲኖረው የግድ ይላል:: ክብርና ድንቅ የሆነውን ዓላማ አንግቢአለሁ የሚል ማነኛው ታጋይ፥ ከፍተኛውን የሞራል አምባ ሊይዝ ይገባዋል:: የሞራል ጉዳይ በመጥላትና በመውደድ፥ በመሰልቸትና በመድከም፥ በመጠንከርና በመላላት፥ ልጓም ተሸብቦ ሊተረጎምና ሊገለጽ ከቶ የሚገባው ሂደት አይደለም::

" ባተሌ አገልጋይ ሰባት ዓመት ቆይቶ ሲከዳ፥ ማጭድ ሰርቆ ይሄዳል" እንደሚባለው ይትብሃል፥ ሀገርን፥ ድርጅትን፥ ሕዝብን፥ ዓላማን፥ መርሃ-ግብርን ወዘተረፈ..... ጥሎ-ጣጥሎ ፥ ዕምነት ከድቶ፥ ነገር-ዓለሙን ትቶ መሄድ ያልተለመደ ክስተት አይደለም::
በሞራል ሽልታ የማይገዛ ሰው ደግሞ ይህንን ከማድረግ ምንም የሚያግደው ነገር አይኖርም:: በየጊዜው በየድርጅቶች የተከሰተው ክህደትና ፍርሻ ይህንኑ ሃቅ በግልጽ አሳይቷል:: ይህንን ክስተት የፈጠሩት ቡድኖች እነርሱ ሌላውን ለመጉዳት ሲሉ ከሚያደርጉት ተግባር ይልቅ፥ በእጅጉ የጎዱት እነርሱ እራሳቸውን እንደሆነና እንደሚሆን ጊዜ የሚያሳየው ዕውነታ ነው:: ዛሬም ቢሆን በህብረተ- ሰቡ እየደረሰባቸው ያለው የሞራል ፍርድና ትዝብት በቀላሉ የሚታይ አይደለም::

ትግሉን በፅናት ጠብቆ የቀጠለው ኃይል የትግልና የሞራል ልዕልናውን አክብሮ መቀጠሉ ብቻ ይህ ነው የማይባል የኅብረተሰብ ድጋፍና ትብብር ማግኘቱ፥ የማይጠበቅ አልነበረም:: ሁሉንም ነገር ጊዜ ይፈተዋል የሚል አባባል ከዕውነት የራቀ ነው ባይባልም፥ ጊዜ ሁኔታን ይለውጠዋል ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ፥ የተሻለ ሁኔታን ለማምጣት የሚያስችለውን ጊዜ ለማስገኘት የሞራል ከፍተኛ ማማን ይዞ መታገል አማራጭ አይኖረውም ለማለት የሚቻል ነው ብለን እናምናለን::

በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ገብቶ መታገል በየግል በጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን፥ ድርጅትን ለቅቆ መውጣትም እንደዚሁ፥ የየግል ውሳኔ እስከሆነ ድረስ ብዙም የሚያከራክር ሊሆን አይቻልም:: ወደ ድርጅት ሲገባ የተቀላቀሉትን ድርጅት ለማሳደግ፥ ለማጠንከርና ዓላማውን ለመምታት ጥረት እንደሚደረግ ሁሉ፥ ድርጅትንም ለቅቆ ሲወጣ የታገሉበትንና የኖሩበትን ድርጅት እንዳለ ትቶ መሄድ ሲገባ፥ አፍርሶ-አፈራርሶ፥ ቀላልና ከባድ ጉዳት አድርሶ፥ ለጠላት አጋልጦ፥ እራስንም እስከ ማዋረድ ድረስ በሚያደርስ የሞራል ድቅት ደቅቆ መሄድ ግን ነውር ቢሆንም፥ ትላንት -ከትላንት በስቲያ በኢሕአፓ ነበርን የሚሉና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቋላት ለሆነው አምባገነን አገዛዝ ተላጣፊና አገልጋይ የሆኑት ፈፅመውታል:::: ይህ ድርጊት፥ ከሞራል አንፃር ሲታይ፥ የበሉበትን

ወጭት ሰባሪና ያጎረሰን እጅ ነካሽ ያሰኛል:: ይህም ራስን በራስ ከማዋረድ አልፎ ተርፎ በኅብረተሰቡም ዘንድ መዋረድን ያተርፋል:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ አመኔታን አጥቶ የተተፋ ክፍል ደግሞ÷ የሚኖረው ዕጣ ፈንታ ወደ ታሪክ ቆሻሻ ቦታ መወርወር ይሆናል::

በኢሕአፓ ውስጥ ተሰባስቦ÷ ለአንድ ክቡርና ቅዱስ ለሆነ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ዓላማና ራዕይ ሲል የሚታገለው አባል ሁሉ÷ የሁለት መሠረታዊና ዓይነተኛ ባህሎች ተገዥና አክባሪ እንደሆነ በኅሌናው ውስጥ አስገብቶ እንደሚታገል ይረዳዋል:: እነኝህ ሁለት ዓበይት ባኅሎችም: አንደኛው÷ የሚታገልለትን ሕዝብ አኩሪ ታሪክና በህል÷ ሥነምግባርና መስተጋብር አክብሮና ጠብቆ መጓዝ ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ በኢሕአፓ ውስጥ የተጎናፀፈውን የፓርቲ ሥነሥርዓትና መሠረታዊ ፕርንስፕል÷ የአብዮታዊ ባኅሎችንና ባኅርያትን አንግቦና አፍቅሮ በተግባር እየተረጎመ መታገል ነው:: የነኝህ ሁለት አኩሪ ባኅሎች አክባሪና ተገዥ የሆኑ አባላት ስለአሉትም ነው÷ ፓርቲው እስከዛሬ ድረስ ኅልውናውን እስከ-ክብሩ÷ ዓላማውን እስከ-ፅናቱ÷ ትግሉን እስከ አልፋ ኦሜጋው ጠብቆ የሚታገለው:: ይህ ደግሞ የሞራል ብቃትን÷ የማንነት ጥንካሬን÷ የዓላማ ፅናትን÷ የራዕይ ግልፅነትን÷ የመከራ ጊዜ አይበገሬነትን÷ ለአምባገነኖች አለመንበርከክን÷ የተሰውለትን ብሔራዊ ዓላማ ለአላፊ ጠፊ ከንቱ ጥቅም አለመለወጥን ይጠይቃል:: ሁሉም ሲጠቃለል÷ ታዲያ በከፍተኛ የሞራል ልዕልና ስር የሚካተት ነው:: ሞራላቸውን ሽጠው÷ ድርጅታቸውን ከድተው÷ የተሰው ጓዶቻቸውን ደምና አፅም አርክሰው÷ የሄዱት ይታዘንላቸው እንደሁ እንጅ÷ የሚታዘንባቸው አይሆንም:: የነበሩበትን ድርጅት የውስጥ ምሥጢር በአደባባይ መዘክዘክ ደግሞ ከውግዘት አያድንም:: ሞራሉ የላሸቀ ሁሉ እየተንጠባጠበ ይቀራል:: ሞራሉን ከነቃል-ኪዳኑ÷ አደራውን ከነዕምነቱ÷ ዓላማውን ከነራዕዩ ጠብቆና አክብሮ የሚታገለው የመጨረሻ አቸናፊ እንደሚሆን የታሪክ ሃቅ ነው:: ይህ ደግሞ ተደጋግሞ መነገሩ አስፈላጊ ነው:: የተቃዋሚው ክፍል በየጊዜው ሊገጥመው በሚችልው የውስጥና የውጭ ችግር ክስተት ምክንያት÷ ወያኔ ላሜ ወለደች የሚል ወቅታዊ መፈንደቅ ሊሰማው ይችል ይሆናል:: በጽናት ትግሉን በቀጠለው አይበገሬው ኃይል የመጨረሻ ድል አድራጊነት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዥታ አይኖረውም:: በጽናት እየታገሉ የክብር ሞትን መቀበል እንጅ ÷ እየተዋረዱ መኖር÷መኖር ሳይሆን የሞት ሞት ነው:: ይህ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ባኅልና ታሪክ አይደለም::